EPA
የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY



የአዳማ ከተማ

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ስራ ተሞክሮ

መጋቢት/2018 ዓ.ም አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ 1

ክፍል አንድ 2

1. ዓላማ 2

1.1. ዋና ዓላማ 2

1.2. ዝርዝር ዓላማዎች 2

2. አስፈላጊነት 2

3. ወሰን 2

4. የመረጃ አሰባሰብ ስልት 2

5. የሚጠበቁ ውጤቶች፡- 3

ክፍል ሁለት፡- 4

6. አዳማ ከተማ 4

7. በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ 5

7.1. ስራ ከመጀመሩ በፊት አካባቢው የነበረበት ሁኔታ 5

7.2. ችግሩን ለመፍታት የተከናወኑ ቅድመ ሁኔታዎች 6

7.3. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 7

7.3.1. የተከናወኑ የግንዛቤ ሥራዎች 7

7.3.1.1. በግንዛቤ የመጣ ለውጥ 8

7.3.2. ቅንጅታዊ ስራ 9

7.3.3. ቴክኖሎጂ አጠቃቀም 9

7.3.4. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ 10

7.3.5. ደረቅ ቆሻሻን በየአይነቱ የመለየት ስራ 13

7.3.6. የክፍያ ሁኔታ 13

7.3.7. የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታ 14

7.3.7.1. ሶዳበር ጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ቦታ 14

7.3.8. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (land fill) 15

7.3.9. ደረቅ ቆሻሻን መልሶ እና አሻሽሎ መጠቀም 18

7.3.9.1. የኮምፖስት ዝግጅት 19

7.3.9.2. ፕላስቲክን መልሶና አሻሽሎ መጠቀም 20

7.3.9.3. **በመልሶና አሻሽሎ መጠቀም የተገኘ ጠቀሜታ**.....21
7.3.10. **በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ ማህበራት**.....21
7.4. **ሞዴል መንደር**.....22
7.4.1. **ሞዴል መንደር** 1.....23
7.5. **የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት በአዳማ ከተማ**.....25
7.5.1. **መዝናኛ**.....26
7.6. **የኮሪደር ልማት ስራ**.....30
7.7. **ችግኝ ጣቢያ**.....32
7.8. **የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማህበረሰብ**.....34
7.9. **በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰዱ ስራዎች**.....34
ክፍል ሦስት፡- 36
8. **ማጠቃለያ**.....36

መግቢያ

ዜጎች ንጹህ እና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው የኢትዮጵያ ህገመንግስት አንቀጽ 44 ተደንግጓል። በመሆኑም መንግስት የአካባቢ ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚረዱ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። በደረቅ ቆሻሻ የአያያዝና አወጋገር አዋጅ 13/89/2017 መርሆዎች መሰረት ቆሻሻን ከምንፈጩ መቀነስ፣ መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት ማድረግ እና በአግባቡ ማስወገድ፤ የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ፤ የበከለን ማስከፈል እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል።

የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጉድለት የአብዛኞቹ የሀገራችን ከተሞች ችግር እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም መነሻ ምክንያቶች ከሆኑት መካካል የነዋሪው ህዝብ ቁጥር በከተማው መጨመር ሰፊውን ቦታ ይይዛል። በተጨማሪም በቆሻሻ አወጋገድ፣ አስተዳደርና አያያዝ ዙሪያ በነዋሪዎች ዘንድ የሚታየው የግንዛቤ እጥረት ሌላው ነው።

በመሆኑም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ባለመዘርጋቱ እና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በየቦታው ቆሻሻ በመጣሉ ነዋሪዎችን ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እያጋለጠ በማህበረሰቡ ላይ የጤና መታወክ እየፈጠረ ስለሆነ ዋነኛ የቅሬታ ምንጭ እየሆነ ይገኛል። የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በከተሞች የሚከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አሰራር ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ ሌሎች ከተሞች እንዲማሩበት በተለያዩ ዘዴዎች ተደራሽ እያደረገ ይገኛል።

በዚሁ መሠረት በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በማሻሻል ቆሻሻውን ከቤት ለቤት ልየታ ጀምሮ፣ ቆሻሻን ጥቅም ላይ ማዋል እስከ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለውን ሂደት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የተከናወኑ ተግባራት ለሌሎች አስተማሪ ሆነው የሚታዩ ናቸው። እንዲሁም የአረንጓዴ መሰረተ ልማት እንደ የኮሪደር፣መዝናኛ እና የከተማ አረንጓዴ ቦታዎች ሥራ የከተማውን ገጽታ ቀይረውታል። በመሆኑም በአዳማ ከተማ ውስጥ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም በከተማ አረንጓዴ መሰረተ ልማት ስራ የተከናወኑትን ለመልካም ተሞክሮ የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ይህ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ

1. ዓላማ

1.1. ዋና ዓላማ

በአዳማ ከተማ አስተዳደር የተከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ስራዎችን **ለመልካም ተሞክሮ የሚሆኑ ተግባራትን** ቀምሮ ሌሎች ከተሞች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ነው።

1.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በማዘመን አካባቢን ጽዱና አረንጓዴ ለማድረግ ዜጎች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ፣
- ቆሻሻ ሀብት መሆኑን በመረዳት ዜጎች በዚህ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- በከተሞች የሚከናወኑ መልካምና አስተማሪ የሚሆኑ ስራዎችን ማበረታታትና ማስፋፋት፣

2. አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ህገመንግስት አንቀጽ 44 ዜጎች ጽዱና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው በሚል በተደነገገው መሰረት ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ የመኖሪያ አካባቢን ለመፍጠር የሚደረገው እንቅስቃሴ ለልማትና ለሕብረተሰቡ ዕድገት ጠቃሚ ነው። በመሆኑም በአንድ ቦታ የተከናወኑ መልካም ስራዎችን በተሞክሮነት ቀምሮ ሌሎች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ተገቢ ስለሆነ ይህን የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ሰነድ በማዘጋጀት ለሌሎች ከተሞች እንዲስፋፋና እንዲተገበር ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል።

3. ወሰን

የተሞክሮ ቅመራው የተከናወነው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በአዳማ ከተማ አስተዳደር የተከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ስራ ላይ በአሰራር ውጤታማና ማሳያ(ሞዴል) ሆነው በተገኙ ስራዎች ላይ ያተኮረ ነው።

4. የመረጃ አሰባሰብ ሰልት

በመጀመሪያ መረጃን ለማሰባሰብ የሚረዳ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት አስቀድሞ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሩ በኢሜል በመላክ ይዘቱን ቀድመው እንዲያውቁት ተደርጓል። በመቀጠልም

የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንደተሠማራ በቅድሚያ ከከተማ አስተዳደሩ አካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ማዘጋጃ ቤት ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ስለ ተልዕኮው ዝርዝር ሁኔታ በመወያየት የተሻለ ተሞክሮ የሚገኝበት ተብሎ በተመረጠው ቦታ በከተማው አስተዳደር ውስጥ በመንቀሳቀስ መረጃ ተሰባስቧል። መረጃ አሰባሰቡም የተዘጋጀውን ቼክ ሊስት በመጠቀም ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች በማገላበጥ፣የማህበር አባላትን፣የአካባቢ ነዋሪ የሆኑ ተጠቃሚዎችንና ባለሙያዎችን በማነጋገር እና ሥራው በሚከናወንበት ቦታ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል። በማጠቃለያውም ከአዳማ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃና አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመስክ ምልከታው በታዩና በተነሱ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት ተደርጎ ተጨማሪ መረጃም ተወስዷል።



ፎቶ 1፡- መረጃ ሲሰበሰብ

5. የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የተቀመረውን መልካም ተሞክሮ በግብዓትነት በመጠቀም ግንዛቤ ይዳብራል፣
- ይህ መልካም ተሞክሮ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎች በአስተማሪነት ለሌሎች ቀርቦ ይጠቀሙበታል፣
- ሌሎች ከተሞችና አካባቢዎች ይህንን ተሞክሮ በግብአት በመጠቀም አካባቢያቸውን ጽዱና ንጹህ ያደርጋሉ

- ሌሎች ከተሞች ይህንን ተሞክሮ በግብአትነት በመጠቀም አካባቢያቸውን በማልማት አረንጓዴ ያደርጋሉ
- ቆሻሻ በቴክኖሎጂ ወደ ጠቃሚ ነገር ተቀይሮ ሀብት መሆኑን ሕብረተሰቡ በተግባር ይረዳል፣

ክፍል ሁለት፡-

6. አዳማ ከተማ

አዳማ ከተማ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በ8^0 33^{11} - 8^0 36^{11} ኬክሮስ ሰሜን እና 39^0 11^1 57^{11} - 39^0 21^1 15^{11} ኬንትሮስ ምስራቅ ላይ ትገኛለች።ከተማው የተመሠረተው በ1908 ዓ.ም.የኢትዮ-ጂቡቲ ባቡር መሥመር መስፋፋትን ተከትሎ እንደነበር ይነገራል።በከተማው የአርሲ፣የባሌ እና የሀረር መስመር የሚተላለፍበት በመሆኑ ከፍተኛ የትራንስፖርት ፍሰት የሚታይበት ሆኖ የሀገሪቱ የገቢና የወጪ ንግድ የሚጓጓዝበት ነው።በመሆኑም ከተማው የስምጥ ሸለቆዋ የንግድ ከተማ በመባልም ይታወቃል። ከተማው ከአዲስ አበባ በ99 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በደቡብ አርሲ ዞን፣በምስራቅ ቦሰት ወረዳ ፣በምዕራብ ሎሜ ወረዳ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ቆቃ ግድብ ይዋሰናል።የከተማው አየር ፀባይ ትሮፒካል እርጥብና ደረቅ አየር የሚያመዝን ሆኖ በአብዛኛው ወይናደጋ ነው።የሙቀት መጠንም ከፍተኛው ዕለታዊ አማካይ 29.05°C ሲሆን ዝቅተኛው ዕለታዊ የሙቀት መጠን 17.07°C ነው። አመታዊ አማካይ የዝናብ መጠኑም 957.07 ሚ.ሜ ነው። የከተማው ከፍታ ቦታም ከ1580-1900 ሜትር ከባህር ወለል በላይ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የአዳማ ከተማ አስተዳደር ራሱን ችሎ የከተማውን ልማትና ዕድገት ለመምራትና ለማስተዳደር በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን ለአስተዳደር እንዲያመች በሁለት መዋቅራዊ ሥርዓት ማለትም በከተማ አስተዳደርና በማዘጋጃ ቤት ሹም ሆኖ አጠቃላይ ከተማ አስተዳደሩ የሚመራውም በከንቲባ ነው።

የከተማው የቆዳ ስፋት 58,098.36 ሄክታር መሆኑን ከከተማ አስተዳደሩ የተገኘ መረጃ ያመለክታል።እ.ኤ.አ.በ2007 ዓ.ም. በተደረገው የህዝብ ቆጠራ ወንድ 108872 ሴት 111340 በድምሩ 220212 ሲሆን ወ 493,046 ሴ 522,281 ድ 1,015,327 እንደደረሰ ሌላ መረጃ ያሳያል። በ2011 ዓ.ም. በተደረገው ግምታዊ ፕሮጀክሽን አጠቃላይ የህዝቡ ብዛት 435222 እንደደረሰ ይገመታል።የህዝብ ጥግግቱም 14500 ሰው በኪሎሜትር ካሬ ላይ ይገኛል።

በከተማው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርም እየጨመረ ይገኛል።የዚህም ዋንኛ ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ እና ከሌላ ከተማ የሚፈልሱ በርካታ ሰዎች በመኖራቸው ነው።ከተማው በርካታ ኢንዱስትሪዎች በስፋት እያደጉ የሚገኙበት በመሆኑ ሰፊ የሥራ ዕድሎችም እየተፈጠረበትም ይገኛል፡

የዕጽዋት ሽፋኑን በተመለከተ ባሁኑ ጊዜ በከተማው መንገዶች ዳር የተለያዩ ዝርያ ያላቸው ችግኞችን የመትከል እንቅስቃሴም ተጠናክሮ እየቀጠለ ነው። የኮሪደር ልማት ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እየተፋጠነ ስለሆነ የከተማው እድገት እና ውበት እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል።



ፎቶ 2፡- የአዳማ ከተማ ገጽታ በከፊል

7. በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

7.1. ስራ ከመጀመሩ በፊት አካባቢው የነበረበት ሁኔታ

ከዚህ በፊት የአዳማ ከተማ አስተዳደር ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ችግር ያለበት ነበር። ለዚህም መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል ለችግሩ ትኩረት አለመስጠት፣የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ከተሞችን የሚመጥን እድገትን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ያለመዘርጋት የመሳሰሉ ችግሮች ተጠቃሽ ናቸው። በአዳማ ከተማ ቀደም ሲል

የነበረው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ያለጥንቃቄ በዘፈቀደ የሚደረግ፣ ቁጥጥር የሌለው፣ ግንዛቤው ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያልተደረገ እና ደረቅ ቆሻሻን በአይነት የመለየት ስራ ያልነበረበት ስለነበር አካባቢው የተበከለ ነበር። በውስን የንግድ ተቋማት እና ዋና መንገዶች ላይ የጽዳት ስራ ቢሰራም ቆሻሻ የሚጣለው ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ ስለነበር የመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ ነበር። በዚህ መልኩ ይጣል የነበረው ደረቅ ቆሻሻ የከተማውን ገጽታ ከማበላሸቱም በላይ የአየር ብክለት በመፍጠር ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ሆኖ ነዋሪዎችን በእጅጉ ይጎዳ እንደነበር እና እንስሳቶች የወዳደቁ ፌስታሎችን እየበሉ ለሞት የሚጋለጡበት ሁኔታ ነበር።

በተጨማሪም ቆሻሻ ማስወገጃና ማጠራቀሚያ ቦታዎች በበቂ ሁኔታና በጥንቃቄ ያልተደራጁ በመሆኑ የሚመነጨዉ ቆሻሻዎች በየመንገዱና በመኖሪያ መንደሮች ሥርዓት በሌለው ሁኔታ በየቦታው ይጣል ነበር። በተጨማሪም በየመንገዱ የሚገኙ ቦዮች በቆሻሻ ስለሚደፈኑ በዝናብ ወቅት መንገዶች በጎርፍ እየተጥለቀለቁ ለመተላለፍ ያስቸግሩ ነበር። ሕብረተሰቡ ቆሻሻን ለማጽዳት ኃላፊነቱን የሚወስደው አንድ ድርጅት ብቻ (ማዘጋጃ ቤት) ነው ብለው ያምኑ ስለነበር አካባቢን በማጽዳት አይመለከተኝም የሚል እሳቤ ነበራቸው። ከግንዛቤ እጥረት የተነሳም ቆሻሻ ጉዳት ብቻ እንጂ ምንም ጥቅም እንደሌለው ይታሰብ ነበር።

7.2. ችግሩን ለመፍታት የተከናወኑ ቅድመ ሁኔታዎች

በአዳማ ከተማ የሚታየውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ችግር ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። የቆሻሻ አያያዙን ሥርዓት ለማሻሻል የከተማ አስተዳደሩ የተሻለ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት ሲያደርግ በመቆየቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጨባጭ ለውጥ መታየት ችሏል። በአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተቀናጀ መልኩ ተደራጅቶ ስራው መሰራት የጀመረው ከተማ አስተዳደሩ ለአረንጓዴ አሻራና ለአካባቢ ጥበቃ ስራ ትኩረት ከሰጠ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው። አጀማመሩም የከተማው አካባቢ ጥበቃ እና ማዘጋጃ ቤት በመቀናጀት እንዲሁም ሁለት ምክትል ከንቲባዎችን፣ ከአካባቢ ጥበቃ ኃላፊና ባለሙያዎችን፣ ከማዘጋጃ ቤት ኃላፊና ባለሙያዎችን አባላት የያዘ ኮሚቴ በማቋቋም የማስተባበርና የመምራት ስራ እንዲሰሩ በማድረግ የግንዛቤ እና የንቅናቄ ስራ ተሰርቷል ። በዚሁ የንቅናቄ ስራ ላይም የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ተደርጓል። ክልሉም ለከተማው አመራርና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት፣ ዕቀድ ላይ አቅጣጫ በመስጠት፣ እቅድን ገምግሞ ግብረ-መልስ በመስጠት፣ አፈጻፀሙን በመከታተል ድጋፍ መደረጉ ለውጤቱ አስተዋጽኦ አድርጓል።

7.3. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ቀደም ሲል በከተማው የመነጨ ደረቅ ቆሻሻን በተወሰነ መልኩ የማጽዳት ስራ የተሰራ ቢሆንም የተሰበሰበው ቆሻሻ የሚጣለው ባልተደራጀ መልኩ እና ባልተመቻቸ ሁኔታ ነበር። ስርአት ያለው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታም አልነበረም።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝብ ብዛት እየጨመረ፣ የሚፈጠር ቆሻሻም እየጨመረ እና በቆሻሻው ምክንያት እየተፈጠረ ያለው የጤና ችግር ከፍተኛ እየሆነ ሲመጣ መፍትሔ መፈለግ ግድ ስለሆነ የከተማው ማዘጋጃ ቤት መፍትሔ የማፈላለግ ጥረቱን ቀጥሎ የተሰሩትን ቅድመ ዝግጅት እና ጅምር ስራዎችን በመነሻነት በመጠቀም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራው እንዲጠናከር ተደርጓል።

7.3.1. የተከናወኑ የግንዛቤ ሥራዎች

በፊት ከነበረው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተላቆ የተሻለ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ለመፍጠር በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ አካላት የግንዛቤ መፍጠር ስራ ተሰርቷል። በዚሁ መሠረት ለአመራሮች፣ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች፣ ለማህበራት አባላት እና ለማህብረተሰቡ የከተማ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት በሚል ርዕስ ለ356,090 (ወ 177,330 ሴ 178,760) ተሳታፊዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል። በሌላ በኩል ብሮሸርና በራሪ ወረቀት፣ባነር እንዲሁም በሬዲዮ ፋና፣ኦቢኤን ሬዲዮ እና ኢቢሲን በመጠቀም ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ተፈጥሯል።



ፎቶ 3፡- ግንዛቤ ሲፈጠር

7.3.1.1. በግንዛቤ የመጣ ለውጥ

የአዳማ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ስርአት ለማስያዝ የግንዛቤ መፍጠር ስራዎችን አከናውኖ በሕብረተሰቡ አስተሳሰብ ላይ የተሻለ ለውጥ አምጥቷል። ህብረተሰቡ በፊት ከነበረውን አስተሳሰብ ተላቅቆ ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ተገንዝቧል። በፊት የህብረተሰቡ አመለካከት የነበረው ከተማን የማጽዳት ኃላፊነት ያለበት የመንግስት በተለይ የማዘጋጃ ቤት ኃላፊነት እንደሆነ ያስብ ነበር። አሁን ግን የመነጨውን ቆሻሻ የማጽዳት ኃላፊነት ያለበት ራሱ ያመነጨው አካል እንደሆነ ህብረተሰቡ ተረድቶ ወደ ተግባር ገብቷል። ማንኛውም ሰው ላመነጨው ቆሻሻ መክፈል እንዳለበት አምኖበታል። ደረቅ ቆሻሻ ሀብት መሆኑን ነዋሪው አውቆ ያገኘውን ግንዛቤ ወደ ተግባር በመቀየር የመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ችሏል። በተለይ በሞዴል መንደር ያሉ ነዋሪዎች ያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ በያይነቱ በመለየት ለመልሶ እና አሻሽሎ መጠቀም እንዲውል ለሚሰበስቡ ማህበራት በአግባቡ ማስረከብ ችለዋል። በአጠቃላይ የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አያያዙና አወጋገዱ ስርአት ስለያዘ የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ባለመያዝ ምክንያት ሲፈጠሩ የነበሩ ችግሮች ቀንሰዋል።



ፎቶ 4፡- በከተማ ደረጃ የጽዳት ዘመቻ ሲደረግ

7.3.2. ቅንጅታዊ ስራ

የከተማው ማዘጋጃ ቤት እና አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ዕቅዳቸውን በጋራ በማቀድ ስራውን በጋራ እየሰሩ ክትትልና ቁጥጥር እያደረጉ የስራውን ቀጣይነት ማጠናከር እለዋል። በዚህም በተገኘው ውጤት የህብረተሰቡ ተሳትፎም ከፍተኛ ሆኗል።

7.3.3. ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

በአዳማ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን ለመተግበር የሚያገለግሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች፣ በእጅ የሚገፉ ጋሪዎች፣ ትራክተሮች፣ ኮምፓክተሮች፣ ስኪፕ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ግሬደሮች፣ ዶዘር፣ ሮሎ እና ቀልዝ መገልበጫ ማሽን ያሉ ሲሆን ባለቤትነታቸው የከተማው ማዘጋጃ ቤት ነው። እነዚህ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ለመሰረተ ልማት ማከናወኛ እና ለዚሁ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት መተግበሪያ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ጋሪዎቹን እያንዳንዱ ማህበር አንድ አንድ የገዙ ሲሆን ተሽከርካሪ ለማይገባበት ቦታ ይገለገሉባቸዋል። ትራክተሩ የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻን ወደ ግዜያዊ ማቆያ የሚወስድ ሲሆን

ከአዳማ እርሻ ማሽነሪ ኢንዱስትሪ በብድር ማህበራት እንዲያገኙ የተደረጉ ናቸው። አከፋፈሉም 30% ማዘጋጃ ቤቱ ከፍሎላቸው 70% ደግሞ ማዘጋጃ ቤቱ ዋስ ሆኖሏቸው ሰርተው እንዲከፍሉ በማመቻቸት ነው። በመጨረሻም ማህበሩ 30%ቱን ለማዘጋጃ ቤቱ ከፍሎ ንብረቱ የማህበሩ ይሆናል። ስኪፕ ሎደሮቹ የማዘጋጃ ቤቱ ሲሆኑ ገንዳዎቹን ለማጓጓዣ እየተገለገሉበት ይገኛሉ። እነዚህ ማሽነሪዎች በመኖራቸው በቴክኖሎጂ የተደገፈ ተግባራት መከናወን ችሏል። ይህ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ስርዓትም ቆሻሻው በአግባቡ እንዲወገድ እና ጥቅም መስጠት እንዲችል አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዲሁም ቆሻሻ በአግባቡ ከተያዘና ከተጠቀሙበት ሀብት እንደሆነ በተግባር እንዲታይ ረድቷል።

በአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አስተባባሪነት ማህበራት በማቋቋም ወደ ስራ የማስገባት ስራ ተሰርቶ ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ(ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለተጠቃሚ በሽያጭ ማስረከብ ተችሏል። ከዚህ በፊት ኮምፖስት ሲዘጋጅ በአካፋ ይገለበጥ የነበረው አሁን በማሽን በመገልበጥ ስራውን ፈጣንና ቀልጣፋ አድርጎታል። ፕላስቲክን መልሶ መጠቀም እንደሚቻል በመረዳትም ከሌላ ቆሻሻ ለይቶ ጨፍልቆና አሽጎ ለፋብሪካ የማስረከብ ስራ እየተሰራ ይገኛል። ከጎማ መጫኛ፣ጫማ እና ለእንሰሳት መቀለቢያ የሚሆን ገንዳ እንደሚሰራ በማወቅ ሰብስቦ ለሚፈልጉ አካላት የማስረከብ ስራ እየተሰራ ይገኛል። ከአገልግሎት በኋላ የተጣሉ ጣሳዎችና ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች ለሌላ ስራ እንደሚያገለግሉ በመረዳት ከሌሎች ቆሻሻዎች ውስጥ ለብቻ በመለየት ለተረካቢዎች በማስረከብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል ።

7.3.4. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ

በፊት የነበረ ደረቅ ቆሻሻን በዘፈቀደ የትም የመጣል ልምድ አሁን ቀርቶ ከመኖሪያ ቤት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ መጀመሪያ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት(በማዳበሪያ) በግቢያቸው ይጠራቀማል። በመቀጠል ቤት ለቤት በሚሰበስቡ ማህበራት በሳምንት ከአንድ እስከ ሁለት ጊዜ በተመደቡበት ሳይት/ ቦታ በየቤቱ በመንቀሳቀስ የተጠራቀመውን ደረቅ ቆሻሻ በማንሳት ወደ ጊዚያዊ ደረቅ ቆሻሻ መቀባበያ ቦታ ያደርሳሉ። በግል ተቋማት(ድርጅት) የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻም የሚነሳው በነዚሁ ማህበራት አማካይነት ነው። የማንሻ ጊዜውም እንደ ሁኔታው(መጠን) ሲሆን የቆሻሻ መጠን በሚበዛበት ተቋማት በየቀኑ የቆሻሻ መጠን በማይበዛበት ተቋማት ደግሞ በየሁለት ቀኑ ይነሳል። በመንገድ ላይ የሚያጸዱ/የሚጠርጉ ማህበራት በመንገድ ላይ ብቻ በፈረቃ የሚሰሩ ናቸው። ከሌሊቱ 10 ሠዓት እስከ ንጋቱ 12 ሠዓት እና ከሰአት ከ9 ሠዓት እስከ

11 ሠዓት የጽዳት ስራቸውን ያከናውናሉ። የሰበሰቡትን ቆሻሻም ቤት ለቤት ለሚሰበስቡ ማህበራት ያስረክባሉ። በዚህ አሰራርም መንገድ ላይ የሚያጸዱት ማህበራት ቤት ለቤት ለሚሰበስቡት ማህበራት ቆሻሻውን ስለተረከቧቸው በወር 1050 ብር በደረሰኝ ይከፍሏቸውና ባቀረቡት ደረሰኝ መሰረት ክፍያው በማዘጋጃ ቤት በኩል ይወራረድላቸዋል/ይተካላቸዋል።



ፎቶ 5፡- የጽዳት ሰራተኞች በጽዳት ላይ



ፎቶ 6፡- የመንገድ ላይ ጽዳት ገጽታ በከፊል

የቦይ ጽዳት ሰራተኞች አሰራርም ቦዩ በሳይት ተከፋፍሎ ለያንዳንዱ የቦይ ጽዳት ማህበራት በኮንትራት በማከፋፈል እንዲያጸዱ ተደርጓል። ስምምነታቸውም በማንኛውም ጊዜ ማጽዳት

ይችላሉ ግን ቦዩ ሁሌም ንጹህ መሆን አለበት በሚል ስምምነት ገብተው ነው። በተጨማሪ ድርጅቶች እስከ 50 ሜትር ርቀት ውስጥ ክፊትለፊታቸው የሚገኘውን ቦታ እንድያፀዱ ተደርጓል። የተጸዳው ቆሻሻ ወዲያውኑ ተነስቶ በመዘጋጃ ቤቱ አጓጓዥነት ቀጥታ ወደ ማስወገጃ ቦታ ተወስዶ ይጣላል።

በቦይ ጽዳት ላይ የሚሰሩ በ22 ማህበራት 220 አባላት እንዲደራጁ በማድረግ የሙያ ብቃታቸው በምዘና እንዲረጋገጥ ተደርጎ ወደ ስራ ተሰማርተዋል።



ፎቶ 7፡- የቦይ/ዲች ጽዳት በከተማው

7.3.5. ደረቅ ቆሻሻን በየአይነቱ የመለየት ስራ

የደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራው የሚከናወነው በተለያየ ቦታ ሲሆን በሞዴል መንደሮች በየቤቱ ልየታው ይከናወናል። ከሌሎች መንደር እና ከተቋማት የመነጨ ደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራው ላይ ክፍተት ስላለው ቆሻሻው ወደ ኮምፖስት ሼድ ተወስዶ የመለየት ስራ ተሰርቶ የሚበሰብሰውን እዛው ለኮምፖስት ዝግጅት በመጠቀም ለመልሶና አሻሽሎ መጠቀም የሚሆኑትን ወደሚፈለግበት ቦታ በማስረከብ ቀሪው የማይፈለገው ደግሞ ወደ ማስወገጃ ቦታ ይላካል። የፍርስራሽ ቆሻሻ ለተለያየ ምክንያት የተቆፈረ/የተቦረቦረ ቦታን (quarrying site) መሙሊያነት እየተገለገሉበት ይገኛል።



ፎቶ 8፡- ቤት ለቤት የተለየ ደረቅ ቆሻሻ

7.3.6. የክፍያ ሁኔታ

ይህ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ሲጀመር ማዘጋጃ ቤቱ ከማህበራት ጋር ውል ተዋውሎ ሲሆን ሕብረተሰቡም ድርሻው ምን እንደሆነ እና ድርሻውን መወጣት እንዳለበት ግንዛቤ ተፈጥሮለት ነው። በመሆኑም ሁሉም ማሕበራት እንደየስራ ድርሻቸው ግዴታቸውን ሲወጡ የህብረተሰቡ እና የተቋማት ግዴታ ከሆነው ውስጥ አንዱ ደግሞ ወርሀዊ ክፍያ ነው። በዚህ መሰረት አንድ አባወራ እንደ ቆሻሻው መጠን በወር ከ50 እስከ 200 ብር ሲከፍሉ ድርጅት ደግሞ ከ300-2000 ብር በወር ይከፍላሉ።

አከፋፈሉን በተመለከተ ህብረተሰቡ ከመኖሪያ ቤት ጣራና ግድግዳ ግብር ጋር የሚከፍሉ ሲሆን ድርጅት ደግሞ ከስራ ግብር ጋር ይከፍላሉ። የመንግስት ተቋማት ግን አይከፍሉም። በተለያዩ ፕሮግራሞች ምክንያት የተለየ ቆሻሻ ከመነጨ በስምምነት በልዩ ክፍያ እንዲነሳ ይደረጋል።

7.3.7. የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታ

በአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ ግዚያዊ ማቆያ ቦታዎች ያሉ ሲሆን ቆሻሻው ወደ ማስወገጃ ቦታ ከመድረሱ በፊት በዚህ ቦታ ደርሶ የመለየትም ስራ ይከናወናል። ካሉት ግዚያዊ መቀባባያ ቦታዎች ውስጥም ሶዳበር የሚባል ቦታን ለናሙናነት ማየት ተችሏል።

7.3.7.1. ሶዳበር ጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ቦታ

ይህ ቦታ የሚገኘው በደንበላ ክ/ከተማ ኢሬቻ ወረዳ ሲሆን ቴድሮስ፣ ይደግና ጓደኞቹ በሚባል ማህበር የተደራጁ አባላት በቦታው ላይ ስራውን እያከናወኑ ይገኛሉ። በዚህ የደረቅ ቆሻሻ ጊዚያዊ መቀባበያ ቦታ በሚሰበስቡት ማህበራት የሚመጣው ደረቅ ቆሻሻ በተወሰነ መልኩ የመለየት ስራ ይሰራና ወደሚፈለገው እና ወደ ማስወገጃው ቦታ ይተላለፋሉ።



ፎቶ 9፡- ለብቻ የተለየ ፕላስቲክ

በሌላ በኩል ተመልሰው ለሌላ አገልግሎቶች የማይውሉ የግንባታ ፍርስራሾችና ከዲች ውስጥ የጸዳ ደረቅ ቆሻሻ ጊዚያዊ መቀባበያ ቦታ ሳይደርስ በቀጥታ ወደ ማስወገጃ ቦታ ተወስዶ ይጣላል። በጊዚአዊ መቀባበያ ቦታ ቆሻሻው ይሰበሰብና ማሽን ሲገኝ ወዲያው የሚነሳ ሲሆን የማሽን እጥረት ሲያጋጥም ደግሞ እስከ ሳምንት ይቆያል።

7.3.8. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (land fill)

በፊት በአዳማ ከተማ አስተዳደር ደረጃውን የጠበቀ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ባለመኖሩ በአዲስ አበባ መግቢያ ዋና መንገድ አጠገብ በጠባብ ቦታ ላይ ከከተማው የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ ይጣል ነበር። ይሄም በከተማው ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽኖ አሳርፎ ለአካባቢው ብክለት መንስኤ በመሆን የሰው ልጅ የጤና ችግር እየፈጠረ ነበር።



ፎቶ 10፡- በፊት የነበረው ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ

አሁን በአዳማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ (land fill) ቦታ በአዲስ ሁኔታ ተሰርቶ ስራ ጀምሯል።



ፎቶ 11፡- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መግቢያ

ቦታው ሲመረጥ በመስፈርትነት የታየው ከህብረተሰቡ የራቀ መሆኑ፣ ቆሻሻን ለማስገባት መንገዱ ምቹነት ያለው መሆኑ፣ የነፋስ አቅጣጫው ወደ ከተማው ነዋሪዎች የማይሄድ መሆኑ፣ ከወንዝ ዳርቻ የራቀ መሆኑ እና መሬቱ ለእርሻና ግጦሽ የማያገለግል መሆኑ ታይቶ የተመረጠ ነው። ማስወገጃ ቦታው የሚገኘው ከሕብረተሰቡ መኖሪያ ቤት ርቆ የሚገኝ ሲሆን በመንግስት (በማዘጋጃ ቤቱ) ባለቤትነት የሚተዳደር ነው። የቦታው ክልል ስፋትም 30 ሄክታር ነው። ቦታው በ2017 ዓ.ም ተመርቆ ከመስከረም 2018 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ይገኛል።



ፎቶ 12፡- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ

ይህ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ቀጣይነት ባለው መልኩ አገልግሎት እንዲሰጥ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ይገኛል። በቂ ማሽን ተሟልቶ በአግባቡ እንዲጠቀጠቅ በዕቅድ ተይዟል። እዛው ግቢው ውስጥ ለአሻሸሎና መልሶ መጠቀም፣ ለመጋዘን፣ ለልየታ እና የኮምፖስት ማዘጋጃ ታስቦ ሼድ ተሰርቷል። በዚህ ቦታ የተለያየ የስራ ድርሻ ያላቸው የሰው ኃይልም ይገኛል። እነሱም በጥበቃ፣ በአስተባባሪነት እና በመረጃ መያዝ ስራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን ወ 4 ሴ 3 ድ 7 በቦታው ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው። በተዘጋጀው ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ውስጥ ከቆሻሻው የሚወጣውን የሙቀት አማቂ ጋዞች በዋናነት ሚቴን ጋዝ ሰብስቦ እና ተቆጣጥሮ ወደ ኃይል(ፓወር) የሚቀይር ቴክኖሎጂ የተሰራ ሲሆን አገልግሎት መስጠት አልጀመረም።



ፎቶ 13፡- በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ግቢ የተሰሩ ሼዶች

በግቢው ውስጥ እየተከናወነ ያለው የማስወገድ ስራ ብቻ ሳይሆን ደረቅ ቆሻሻን በየአይነቱ የመለየት እና ኮምፖስት የማዘጋጀት ስራም እየተከናወነ ይገኛል።



ፎቶ 14፡- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግቢ በልየታ ላይ ያሉ ቆሻሻዎች

7.3.9. ደረቅ ቆሻሻን መልሶ እና አሻሽሎ መጠቀም

ለመልሶ መጠቀም እና ዑደት ስራ የሚለየው ደረቅ ቆሻሻ (ፕላስቲክ፣ ብረታብረት፣ ወረቀት፣ ካርቶን እና ወ.ዘ.ተ) ሲሆኑ በከተማው ደረቅ ቆሻሻን አሻሽሎ እና መልሶ ከመጠቀም አንጻር ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ የኮምፖስ ዝግጅት እየተዘጋጀ ይገኛል። እንዲሁም በተደራጁ ማህበራት የፕላስቲክ ጠርሙስን በመለየት እና በማሽን ጨፍልቆ በማሸግ ወደ ሌላ ፋብሪካ እየተላከ ይገኛል። ተረካቢ ፋብሪካውም ፕላስቲኩን ወደሌላ ጠቃሚ እቃ አሻሽሎ በመስራት አገልግሎት እንዲሰጥ እያደረገ ይገኛል። ፕላስቲክ ጠርሙሶች በመልሶ መጠቀም ለፈሳሽ ሳሙና መያዣነት አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ ይገኛል። በማህበራት የተደራጁ አባላትም ቆሻሻውን ወደ ሀብትነት በመቀየር የገቢ ምንጭ ማግኘት ችለዋል።

በየቦታው ተጥሎ አካባቢን ሲበክል የነበረውን የማይበሰብስ ቆሻሻ በአሻሽል መጠቀም ተለውጦ ለሌላ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። ቆሻሻ የነበረው ጎማ ለመጫኛ፣ ለእንስሳት መቀለቢያ ገንዳ፣ ለጫማ እንዲውል በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። የተለያየ አገልግሎት ሰጥተው የተጣሉ ብረታ ብረቶች ለቆራሊዮ የማስረከብ ስራ እየተሰራ ለሌላ እቃ ዝግጅት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

7.3.9.1. የኮምፖስት ዝግጅት

በአዳማ ከተማ ስፋቱ 286 ካ.ሜ የሆነ የኮምፖስት ማዘጋጃ ቦታ (ሳይት) በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል። የኮምፖስት ማዘጋጃ ቦታ (ሼድ) ውስጥም የሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻን በግብዓትነት በመጠቀም በዘመናዊ አሰራር ኮምፖስት እየተዘጋጀ ይገኛል። የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በአዳማ ከተማ ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳሉ ተብለው ከተቋቋሙ ማህበራት ውስጥ ሁለቱ ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ(ኮምፖስት) የሚያዘጋጁ ማህበራት ናቸው። እነሱም አዲስ ራዕይ ደረቅ ቆሻሻ መልሶ ማልማት እና ግሪን ኢትዮጵያ ፅዳትና መልሶ ማልማት ናቸው። እነዚህ ማህበራት የመጣላቸውን ደረቅ ቆሻሻ በመለየት ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት በማምረት (ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሃብትነት በመቀየር) እና ያመረቱትን በመሸጥ ተጠቃሚ ሆነዋል። ሁለቱም ማህበራት እያንዳንዳቸው 10 አባላት ያላቸው ሲሆን በድምሩ 20 አባላት በስራው ተሰማርተው እየተጠቀሙ ይገኛሉ። ሁለቱም ማህበራት እየሰሩ ያሉት ጎን ለጎን በአንድ ሼድ ውስጥ ሲሆን የሁለቱም የአሰራር ስርአታቸው ተመሳሳይ ነው። ኮምፖስቱንም የማገላበጥ ስራ የሚሰራው በማሽን ሲሆን የሚነፋበት ወንፊትም በሰው ጉልበት ሳይሆን በኤሌክትሪክ ኃይል ነው።



ፎቶ 15፡- የተዘጋጀ ኮምፖስት

7.3.9.2. ፕላስቲክን መልሶና አሻሽሎ መጠቀም

በተለያየ ቦታ ያለአግባብ ተጥለው አካባቢን እየበከሉ ካሉት ደረቅ ቆሻሻዎች ውስጥ አንዱና ዋንኛው የፕላስቲክ ቆሻሻ ነው። የፕላስቲክ ቆሻሻ ለብዙ አመታት ሳይበሰብስ የሚቆይ ሲሆን አፈርን፣ ውሃን እና አየርን ከመበከልም አልፎ እንስሳቶች ከሌላ ምግባቸው ጋር አብረው ሲበሉት በጤናቸው ላይ እንከን ይፈጥራል። በአጠቃላይ የፕላስቲክ ቆሻሻ በእጽዋትም ሆነ በእንስሳት እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብታችን እንደ አፈር፣ ውሃና አየር ላይ ብክለት በመፍጠር ለጤንነታችን ጠንቅ ሆኖ ይገኛል።

በመሆኑም የአዳማ ከተማ አስተዳደር የፕላስቲክ መልሶና አሻሽሎ መጠቀም ቴክኖሎጂን በመጠቀም ይህንን ችግር ለመቅረፍ እየሰራ ይገኛል። ከተማውን በዋናነት እያቆሸሹ ያሉት የፕላስቲክ ቆሻሻዎች የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ጠርሙሶች፣ጀሪካን፣ ማዳበሪያና የተለያዩ የፕላስቲክ እቃዎች ስብርባሪ ሲሆኑ በማህበራት እና በግለሰቦች እንዲሰበሰቡ በማድረግ መልሰው ለሚጠቀሙና ዑደት ለሚያደርጉ ድርጅቶችና ካምፓኒዎች በማስረከብ ደረቅ ቆሻሻ ወደ ሀብትነት እንዲቀየር እየተሰራ ይገኛል።

በከተማው ቆሻሻን የመልሶና አሻሽሎ መጠቀም ስራ ላይ የተሰማሩ ማህበራት ያሉ ሲሆን ካሉት ውስጥም በአንዱ የስራ ቦታ እየተሰራ ያለውን መመልከት ተችሏል። በዚህ ቦታ ላይ በፊት እየሰሩ የነበሩት ሆጂኔ ሀጉደኑ እና ገመቹ የሚባሉ ማህበራት ነበሩ። አሁን ግን እነሱ አቋርጠው በቦታው ላይ ሌላ ሦስት (3) ወንድ አባላት የያዘ ማህበር ቢኒያም፣ ፍሬዘርና ጓደኞቹ በሚል ስያሜ ተደራጅቶ ስራውን እያከናወነ ይገኛል። ይህ ማህበር ስራውን የጀመረው በጥቅምት ወር በ2018 ዓ.ም ሲሆን አሁንም በስራ ላይ ይገኛል። የዚህ ማህበር አባላት 1 ኪ.ግ ፕላስቲክ በ20 ብር ተረክበው የፕላስቲክ ጠርሙሱን በመጨፍለቅና በ40 ኪ.ግ ክብደት በማሰር ለተረካቢዎች 1 ኪ.ግ 33 ብር ያስረክባሉ። ማህበሩ አንድ የፕላስቲክ ጠርሙስ መጨፍለቂያ ማሽን ያለው ሲሆን በቀን ከ2000-3000 ብር የሚፈጅ ፕላስቲክ እንደሚረከቡ እና ከ10 እስከ 12 እስር ያመርታሉ።



ፎቶ 16፡- በማህበሩ እየተሰራ ያለው የፕላስቲክ አሻሽሎ መጠቀም ስራ

7.3.9.3. በመልሶና አሻሽሎ መጠቀም የተገኘ ጠቀሜታ

በአዳማ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ የመልሶና አሻሽሎ መጠቀም ስራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ማግኘት ተችሏል። ከጠቀሜታዎቹ ውስጥም፡-

- **ለበርካታ ሴቶችና ወጣቶች የስራ ዕድል ተፈጥሯል**
- **አካባቢን እየበከለ ለጤና ጠንቅ የነበረ ቆሻሻ ወደ ሀብትነት ተቀይሮ የገቢ ምንጭ ማስገኘት ችሏል**
- **ወደ ማስወገጃ ቦታ የሚጓጓዝ ቆሻሻ መጠን እንዲቀንስ በማድረግ የማስወገጃ ቦታው ቶሎ እንዳይሞላ አስተዋፅኦ አድርጓል።**
- **ወደ ማስወገጃ ቦታ የሚጓጓዝ ቆሻሻ መጠኑ በመቀነሱ የማጓጓዣ ወጪ እንዲቀንስ ረድቷል።**

7.3.10. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ ማህበራት

በአዳማ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ በርካታ ማህበራት ያሉ ሲሆን ቤት ለቤትና ከድርጅት ደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብ፣ የመንገድ ላይ ቆሻሻ ጽዳት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ (ዲች) ውስጥ ጽዳት፣ ደረቅ ቆሻሻን የመለየት፣ የኮምፖስት ዝግጅት፣ ፕላስቲክ መልሶና አሻሽሎ መጠቀም ላይ የሚሰሩ እና ሌሎችም ማህበራት ናቸው። እነዚህ

ማህበራት ሁሉም የየራሳቸው አባላት ያሏቸው ሲሆን ከከተማው ማዘጋጃ ቤት ጋር ውል ተዋውለው በውላቸው መሰረት ስራቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ።

ቤት ለቤትና ከድርጅት ደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብ ስራ የሚሰሩ 54 ማህበራት ሲኖሩ 540 አባላት አላቸው። የመንገድ ላይ ቆሻሻ ጽዳት ስራ የሚሰሩ 60 ማህበራት ሲኖሩ 600 አባላት አላቸው። የዲች ውስጥ ጽዳት ስራ የሚሰሩ 22 ማህበራት ሲኖሩ 220 አባላት አላቸው። ፕላስቲክ መልሶና አሻሽሎ መጠቀም ስራ የሚሰሩ 4 ማህበራት ሲኖሩ 260 አባላት አላቸው። በደረቅ ቆሻሻ የማጓጓዝ ስራ የሚሰሩ ማህበራት ያሉ ሲሆን 360 አባላት አላቸው። በማስወገጃ ቦታው የሚሰራ 1 ማህበር ያለ ሲሆን 7 አባላት አሉት።

7.4. ሞዴል መንደር

በአዳማ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም አካባቢያቸውን በጽዳት በመያዝና በማልማት እንቅስቃሴአቸው ታይቶ ከ2013 እስከ 2017 ዓ.ም 97 እና በ2018 ዓ.ም 89 በድምሩ 186 ሞዴል መንደሮች ተመርጠዋል። በ2018 ዓ.ም የተፈጠሩ ሞዴል መንደሮች የበዙበት ምክንያት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በንቅናቄ እና በዘመቻ ስለተንቀሳቀሱ ነው።

በእነዚህ ሞዴል መንደሮች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ራሳቸውን በማደራጀት ወደ ልማት በመሰማራት፣ አካባቢያቸውን በጋራ በፕሮግራም በማፅዳት፣ ከግቢያቸው ውጪ ከ20 እስከ 30 ሬድየስ ጽዱና አረንጉዴ በማድረግ፣ የሚነገራቸውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተቀብለው በመጠቀም፣ በግል ግቢያቸው ውስጥ የአረንጓዴ ልማት በማልማት እና ከሌሎች መንደሮች የተሻሉ ሆነው ስለተገኙ ሞዴል መንደር ተብለው ሊመረጡ ችለዋል።



ፎቶ 17፡- የሞዴል መንደሮች ገጽታ በከፊል

7.4.1. ሞዴል መንደር 1

ይህ መንደር የሚገኘው ቀበሌ 11 በሚባለው ቦታ ሲሆን ከተመረጡት ሞዴል መንደሮች ውስጥ ይህን መንደር በአካል ማየት ተችሏል። በዚህ መንደር አካባቢ ያሉ መንገዶች ጽዳታቸው የተጠበቀ ነው።




ፎቶ 18፡- የሞዴል መንደሩ ስፍራ በከፊል

በየአጥሮቹ ዳርቻ የተለያዩ አረንጓዴ ተክሎች ተተክለው ለመንደሩ ውበት ሆነዋል። በመንገዱ ዳርቻ ያሉት አረንጉዴ እጽዋቶች በቅርጽ ተከርክመው ለእይታ ማራኪ ናቸው። በመንገዱ ዳርቻ ላይ ካሉት አረንጉዴ እጽዋቶች ጋር የተለያየ ቀለም ያላቸው አበቦች ያሉ ሲሆን የተፈጥሮ ሽቶን በነፃ ይጋብዛሉ።

በሞዴል መንደሮች የግለሰቦቹ ግቢ ጽዳቱ የተጠበቀ ነው። የመነጨ ደረቅ ቆሻሻ እስኪነሳ ድረስ በደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት (በማዳበሪያ) የሚበሰብስ እና የማይበሰብስ በሚል በየአይነቱ ተለይቶ ይቀመጣል። በግቢያቸው ውስጥ የተለያዩ ተክሎች አልምተዋል።

በዚህ መንደር ልማቱ ሲሰራ የሚያስተባብሩ እንዳሉ፣ ሁሉም በመተባበር በተነሳሽነት እንደሚሰራ፣ ስራው መጠናከር የጀመረው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ፣ ግቢንና አካባቢን ማፅዳት ጥቅሙ የራስ መሆኑን አውቀው አሁንም የተቀናጀ ስራው እንደቀጠለ መሆኑን፣ ቆሻሻን

በአይነቱ የመለየት ስራም እንደሚያከናውኑ እና አካባቢያቸው በአረንጓዴ እንዲዋብም እየሰሩ በሆኑን በተግባር ማየት ተችለዋል።



ፎቶ 19 ፡- አቶ መሀመድ ሰይድ ስለ መንደራቸው የጽዳት ስርዓት ሲያብራሩ

7.5. የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት በአዳማ ከተማ

በአዳማ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት በስፋት ተሰርቶ የከተማውን ውበት ከፍ አድርጎታል። በሞዴል መንደሮች የተሰሩ አረንጉዴ ልማቶች፣ በተለያየ ቦታ የተሰሩ መዝናኛዎች(መናፈሻዎች) እና የኮሪደር ልማቶች በፊት የነበረውን ቆሻሻ እንዲጠፋ አድርገው የከተማውን ገፅታ ወደ ማራኪና መዝናኛ ቀይረውታል። ልማቱ የተሰራው በአንድ አካል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ነው። ልማቱ በመንግስት፣ በማህበራት፣ በድርጅቶች፣ በህብረተሰቡ እና በግለሰቦች አንድነትና ርብርብ በመሰራቱ የሚጠበቀውን ውጤት አስመዝግቧል። ለልማቱ መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ በርካታ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ያሉ ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ **አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ፣ የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ፍቃዱ ገመቹ (ግለሰብ) እና የአዳማ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ቢሮ የሚጠቀሱ ናቸው።**

የአዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ግቢያቸውን እና ከግቢያቸው ውጪ አዳማ ቆርቆሮ ሰፈር የሚባለውን በተጨማሪ በማልማት የከተማው ውበት እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል።

የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ደግሞ የአሰላ ፈጣን መንገድ ማሳለጫ/መተላለፊያ በውስጥ በኩል ያለውን አልምቶ የአካባቢው ውበት ማራኪ እንዲሆን አድርጓል።


ፍቃዱ ገመቹ የሚባል ግለሰብም የአሰላ ፈጣን መንገድ ማሳለጫ/መተላለፊያ በውጪ በኩል ያለውን በፍላጎት አልምቶ የአካባቢው ውበት እንዲጨምር በማድረግ አስረክቧል።

የአዳማ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ቢሮ በአንጋቱ ወረዳ ያለውን መናፈሻ/መዝናኛ ሰርቶ ለከተማው ውበትና ለማህበረሰቡ መዝናኛ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

7.5.1. መዝናኛ

በአንጋቱ ወረዳ ያለው መናፈሻ/መዝናኛ የተሰራው በአዳማ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ቢሮ ሲሆን ደጋጋ ፓርክ በመባል ተሰይሟል። ይህ መዝናኛ ቦታ የሚገኘው በወንጂ ማዞሪያ አካባቢ ሲሆን ከመልማቱ በፊት በከፍተኛ ሁኔታ የተለያየ ቆሻሻ የሚጣልበት ቦታ ነበር። በዚያም አካባቢ የነበረው ሽታ በአካባቢው ለሚኖሩ ህብረተሰቡ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ለሚተላለፉ ሰዎችም ጤና ጠንቅ ሆኖ ነበር። አሁን ግን ሲታይ (መጋቢት/2018 ዓ.ም) ያሁሉ ቀርቶ በቦታው ላይ የተለያዩ ጠቃሚ እና የሚያዝናኑ ነገሮች ይገኛሉ። ልማቱ የተሰራውም ለአዳማ ኢቨስትመንት ግሩፕ ኮንትራት (out source) ተሰጥቶ ነው።

በግቢው ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከነዋጋቸው በዝርዝር ተቀምጠዋል



ፎቶ 20፡-የአገልግሎት አሰጣጥ ዝርዝር

በግቢው ውስጥ የተለያዩ የውበት ዛፎች እና ሳር ስላለ ግቢውን አረንጓዴ መዝናኛ ማለት ያስችላል።



ፎቶ 21፡- መዝናኛ ስፍራ በከፊል



ፎቶ 22፡- የሚገኙ መዝናኛ መቀመጫና ጎጆዎች በከፊል

በግቢው ውስጥ በተለያየ ቦታ የሚፈነጨው እና የሚረጨው የውሃ ውበት/ፋውንቴን የአካባቢው ስነምህዳር ለጤና ምቹ እንዲሆን አድርጎታል።

ለህፃናት መጫወቻ የሚሆን የተዘጋጀ ቦታ እና ብስክሌት ስላሉ ታዳጊዎችን ታሳቢ ያደረገ መዝናኛ እንደሆነ ራሱ ግቢው ይመሰክራል።





ፎቶ 23፡- የሚገኙ የህጻናት መጫወቻ በከፊል

በግቢው ውስጥ የሻይ ቡና አገልግሎት እየተሰጠ ስለሆነ በፈለጉት መንገድ ለመዝናናት እድሉ ሰፊ ነው።



ፎቶ 24፡- በግቢው ውስጥ ያለ ካፍቴሪያ

ግቢው መጸዳጃ ቤት እና መታጠቢያ ቤት(ሻወር) በተሟላ ሁኔታ ስላለው እዛው መጠቀም መታጠብ ይቻላል።



ፎቶ 25፡- በግቢው ውስጥ ያለ መፀዳጃ ቤት

7.6. የኮሪደር ልማት ስራ

የኮሪደር ልማት ፅንሰ ሀሳቡ የሚያጠነጥነው ነባር ከተማን በማደስ የከተማውን ገፅታ በማሻሻል ለኑሮ ምቹና ማራኪ እንድትሆን ማድረግ ነው። በሂደቱም ሰፋፊ ግንባታዎች የሚከናወኑበት ነው። በዚህም መሠረት የመንገድ መሠረተ ልማትን በማሻሻል ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶችን በግራና በቀኝ ደረጃውን የጠበቀ ማድረግ፣ ማየት ለተሳናቸው ሰዎች የሚሆን መንገድ መስራት፣የብስክሌት ማሽከርከሪያ መንገድ መፍጠር፣ በርካታ መኪናዎችን ማስተናገድ የሚችሉ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያዎችን (ፓርኪንጎችን) መገንባት እና የመሳሰሉ ተግባራትን ያቀፉ ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በሌላ በኩልም መደበኛ የመንገድ መብራት መሠረተ ልማት ሥራዎችን ማዘመን ሲሆን የደህንነት ካሜራ ያላቸው ስማርት ፖሎች፣ የመሳሰሉት

ተግባራት ይከናወናሉ። በተጨማሪም የህዝብ መገናኛዎችንና ማረፊያዎችን፣የውሃ ፏፏቴዎችን፣ዘመናዊ የመንገድ ዳር መፀዳጃ ቤቶችን የመገንባት ሥራንም የሚያጠቃልል ነው። በዚሁ መሠረተ በአዳማ ከተማ ተገቢውን የግንዛቤ ስራ በመስራት የኮሪደር ልማት ስራ ተጀምሮ እየተሰራ ይገኛል። በመሆኑም እስከ አሁን በከተማው በሁለት ዙር የኮሪደር ልማት የተሰራ ሲሆን የአንደኛው ዙር ተጠናቆ ሁለተኛው ዙር ወደ መጠናቀቅ ተቃርቧል።

በ1ኛው ዙር የተሰራው ከገልማ አባገዳ አዳራሽ እስከ አመዴ ግብርና አካባቢ ሲሆን አካባቢው ከመጽዳትም አልፎ ውበቱ ጨምሯል።



ፎቶ 26፡- የኮሪደር ልማት በከፊል

በ2ኛው ዙር ደግሞ በሁለት መስመር ላይ የተሰሩ ሲሆኑ መጠናቀቅ የቀራቸው አሉ። የተሰሩትም አንደኛው መስመር ከፈጣን መንገድ እስከ ገልማ አባገዳ አዳራሽ የተሰራ ኮሪደር ልማት ነው።



ፎቶ 27፡- የኮሪደር ልማት በከፊል

ሁለተኛው መስመር የተሰራው ከምስራቅ ሸዋ ግብርና ጽ/ቤት(አመዴ) እስከ ፈጣን መንገድ መውጫ(ኩርፋ) ያለው የኮሪደር ልማት ነው። በዚህ ኮሪደር ስራ ለአስፓልት ስራው ማስፈፀሚያ በጀት የቻለው በፌዴራል በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር (ERA) ሲሆን ለቀሪው ስራ ማስፈፀሚያ በጀት የቻለው ደግሞ የአዳማ ከተማ አስተዳደር ነው። በግራና ቀኝ የፍሳሽ ማስወገጃ ዲች፣ የእግረኛ መንገድ፣ የሳይክል መንገድ፣ መብራት፣ አረንጓዴ ልማት፣ፓርኪንግ አና የመሳሰሉት የተሰሩት በማዘጋጃ ቤቱ ለአዳማ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኮንትራት ሰጥቶ ነው። የሁለቱም ዙር የኮሪደር ልማት ስራ 13.76 ኪ.ሜ ይሆናል። ይህ የኮሪደር ልማት መሰራቱ አካባቢው ጽዱና ውብ፣ አየሩ ለጤና ምቹ፣ለእይታ ማራኪ እና ለመንቀሳቀስ ምቹ ስለሆነ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ለህብረተሰቡ አበርክቷል።

7.7. ችግኝ ጣቢያ

ለአረንጓዴ ልማት ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ ችግኝ ጣቢያ ዋንኛው ነው። የኮሪደር ልማት፣ መዝናኛ ቦታ እና ሞዴል መንደሮች እንዲዋቡ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ ዋንኛው ችግኝ ጣቢያ

ነው። በአዳማ ከተማ ካሉት ችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ የአዳማ ማዘጋጃ ችግኝ ጣቢያ በአካል የታየ ሲሆን የዚህ ችግኝ ጣቢያ ባለቤት መንግስት (የከተማው ማዘጋጃ ቤት) ሲሆን የሚገኘው በደንበላ ክፍለ ከተማ በኢሬቻ ወረዳ ነው። ችግኝ ጣቢያው ተዘጋጅቶ ስራ የጀመረው በ1998 ዓ.ም ሲሆን ስፋቱ 2 ሄክታር ነው። በዚህ ችግኝ ጣቢያ ውስጥ በተለያየ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ችግኞች አሉ።



ፎቶ 28፡- ከግሪን ሀውስ ውጪ የሚገኙ ችግኞች በከፊል

በዚህ 2018 ዓ.ም የተለያዩ 45 የችግኝ ዝርያ የሆኑ 3 ሚሊዮን ችግኞች ይገኛሉ። በችግኝ ጣቢያው ውስጥ የውበት ችግኞች፣ የጥላ ዛፍ ችግኞች፣ የምግብ(የፍራፍሬ) ችግኞች፣ የከብት መኖ ችግኞች እና ለመድሀኒትነት የሚውሉ ችግኞች ይገኛሉ። የተወሰኑትን ስናይ ወይራ፣ ገራቪሊያ፣ አቡካዶ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ሎሚ፣ ጠጅ ሳር፣ አዝሞሪና፣ የሻይ ቅመም(ናና)፣ጤናዳም እና ሌሎችም ያገኛሉ።



ፎቶ 29፡- የሚገኙ የችግኝ ዝርያዎች በከፊል

በችግኝ ጣቢያው የሚሰራ የሽርክና ማህበር ያለ ሲሆን ወ 4 ሴ 26 ድ 30 አባላት አሉት። ችግኝ ጣቢያው ከችግኝ ማፍላት ጋር የተያያዘ ሙያ ላይ ለሲኦሲ (COC) ማረጋገጫ ስራም እየተሰራ ይገኛል።

7.8. የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማህበረሰብ

በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ምክንያት የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሰዎች በርካታ ናቸው። በማህበራት የተደራጁትን ብቻ ሲታይ ደረቅ ቆሻሻን በማሰባሰብ ስራ 540፣ በመንገድ ጽዳት ስራ 600፣ በደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ ስራ 360፣ በመልሶና አሻሽሎ መጠቀም ስራ 260፣ በዲች ጽዳት ስራ 220፣ በማስወገጃ ቦታ የሚሰሩ 7 እና ሌሎችም የስራ ዕድል አግኝተዋል። ከነዚህ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ከ50% በላይ እና የወጣቶች ተሳትፎ 90% ይሆናሉ።

7.9. በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰዱ ስራዎች

የአዳማ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ የጀመረው በችግሩ አሳሳቢነት ዙሪያ በአመራርና ባለሙያዎች ደረጃ በመወያየት ወደ ቀጣዩ ሂደት በመራመድ ነው።

ከተማ አስተዳደሩ ችግሩን ለመፍታት መነሻ ያደረገው ዕቅድ በማቀድ ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ መፍጠር ነው። በመቀጠልም ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ወደ ዝርዝር ተግባሮቹ በመግባት በተፈጠረው ግንዛቤ መሰረት ወደ ተግባር ተገባ። የሚጠበቀው ውጤት ላይ ለመድረስ ያመች ዘንድ ስራውን ሊያከናውኑ የሚችሉ የተለያዩ ማህበራት በማቋቋም እንዲሁም የሚሰሩበትን ማቴሪያል በማመቻቸት እና ድጋፍና ክትትል በማድረግ ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ አድርጓል።

አመራሩንና ባለሙያዎችን በማጠናከር በስራው ክንውን ላይ የቅርብ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የኃላፊነት ሚናውን ተወጥቷል። አካባቢያቸውን በተሻለ ጽዱ ላደረጉ መንደሮች ሞዴሊ መንደር ብሎ በማበረታታት ለሌላው ምሳሌ እንዲሆኑ አድርጓል።

ከተማ አስተዳደሩ በዚህ ልክ በመስራቱ ከተማው በፊት ካለበት ችግር እና በቆሻሻ መበከል ምክንያት ለበሽታ መጋለጥ ስጋት ከመሆን ተላቆ ዛሬ በሌሎችም ሊጎበኙ የሚችሉማራኪ ስፍራዎች ያለው ከተማ ሆኗል።

በዕቅድ እየተመራ በቅንጅት በመሰራቱ የሚከተሉት ለውጦች/ውጤቶች ተገኝተዋል

- በየቦታው ተዝረክርኮ ከተማውን ይበክል የነበረ ደረቅ ቆሻሻ አሁን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል
- ችግሩን ለመቅረፍ መጀመሪያ ግንዛቤ መፍጠርና በውይይት የመግባባት ስራ መሰራቱ ሁሉም እንዲሳተፍ አድርጎታል
- የግንዛቤ መልእክቶችን በባነር አዘጋጅቶ የጽዳት ዘመቻ በንቅናቄ መሰራቱ ማህበረሰቡን ተነሳሽነት ከፍ አድርጎታል
- በስራው ክንውን ላይ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ድጋፍ፣ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በቅንጅት መሰራቱ ስራውን አቀላጥፎታል
- ማህበራት በማደራጀት የቆሻሻው አያያዝና አወጋገድ በቴክኖሎጂ በመመራቱ ውጤት አስመዝግቧል
- ማህበረሰቡ ባገኘው ግንዛቤ መሰረት ከ20-50 ሬድየስ መንደሩን ማጽዳቱ፣ ቆሻሻን ከቤት ጀምሮ መለየቱ፣አካባቢውን በአረንጓዴ ማልማቱ የታሰበውን ዓላማ አሳክቶታል
- አካባቢያቸውን አጽድተው ያለሙ መንደሮችን በሞዴል መመረጣቸው እነሱን ከማበረታታትም አልፎ ለሌላው አርአያ ሆነው ተነሳሽነትን ይጨምራሉ
- በፊት በየቦታው ተዝረክርኮ የበሽታ መንስኤ የነበረው ደረቅ ቆሻሻ አሁን ሀብት ሆኖ የገቢ ምንጭ ሆኗል
- ከደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ (ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለጥቅም እንዲውል ተደርጓል
- በየቦታው በቆሻሻነት ያስቸግር የነበረ የፕላስቲክ ቆሻሻ በመልሶና አሻሽሎ መጠቀም አገልግሎት መስጠት ችሏል
- አገልግሎታቸውን የጨረሱ የጎማና የብረታብረት ቁርጥራጭ በአሻሽሎ መጠቀም ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ ቆሻሻው ከመነሳቱም አልፎ ለጥቅም መዋል ችሏል
- ሕብረተሰቡ ቆሻሻ ሐብት መሆኑን እንዲያውቁት በተግባር አሳይቷል
- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (Land Fill) ተሰርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል
- በማህበር የተደራጁ ዜጎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል

- **ቆሻሻን በማጽዳት፣ የኮሪደር ልማቶችን በመስራት፣ የውበትና መናፈሻ ስፍራዎችን በመፍጠር እንዲሁም የተለያዩ ችግኞች በማዘጋጀት በአረንጓዴ ልማት አካባቢያቸውን ጽዱና ውብ እንዲያደርጉ ስራ መሰራቱ ለእይታ ከማማሩም አልፎ የአየር ንብረቱ ለጤና ምቹ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።**

ክፍል ሦስት፡-

8. ማጠቃለያ

በአዳማ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ከመጀመሩ በፊት በከተማው የደረቅ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት አልነበረም። በዚህም የተነሳ የከተማው ነዋሪ ከአካባቢው መቆሸሽ የተነሳ ለጤንነት ችግር የተጋለጠ ነበር። በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ ይህንን ችግር በማየትና በመነጋገር የመፍትሄ እርምጃ ወስዶ ውጤት አስመዝግቧል።

የተሰሩት ጠቃሚ ስራዎች ቆሻሻን ማጽዳት ብቻ ሳይሆን በመልሶና አሻሽሎ መጠቀም ቴክኖሎጂ ከቆሻሻ ገቢ በማግኘት፣ በኮሪደር ስራ የከተማን ስታንዳርድ የማሻሻል ስራ በመስራት፣ መዝናኛዎችን በተለያየ ቦታ በመስራት ከተማውን ማስዋብ እና ማህበረሰቡን በማዝናናት፣ ችግኝ ጣቢያዎችን በማጠናከር እና የተለያዩ የእጽዋት ዝርያ ችግኞችን በማዘጋጀት ከተማዋ በአረንጓዴ የተዋበች እንድትሆን አድርገዋታል። ይሔም የከተማ ማጽዳትና ማስዋብ ስራ አካባቢን ከመጠበቅ አንፃር ለሌሎችም ትምህርት ይሆናል።

ስለዚህ ሁላችንም ያለንበትን ቦታ ነባራዊ ሁኔታ በማየትና በማጥናት በቴክኖሎጂ እየታገዝን ተፈጥሮ የሰጠንን ሀብት በአግባቡ በመያዝና በመንከባከብ ተጠቃሚ መሆን አለብን። የአዳማ ከተማ አስተዳደር ውጤታማ የሆነው ሁሉ ነገር ተመቻችቶለት ሳይሆን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመገምገም እና ለችግሩ መፍትሄ በማስቀመጥ በጋራ ታግሎ ያስቀመጠውን ዓላማ በማሳካት ነው። በመሆኑም እኛም "እካባቢያችንን ተንከባክበን ለጤና እና ለኑሮ ምቹ ማድረግ አለብን" በሚል ተነሳስተን አካባቢያችንን በማጽዳት እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሊከሰት ከሚችለው አደጋ ድነን ጽዱ በሆነ ስፍራ መኖር ይጠበቅብናል።